# የእሳት መከላከል

Standard

**ይዘቶች**

1 **መግቢያ** 3

2 **መስፈርቶች** 3

3 **ደህንነታቸው የተጠበቀ የስራ ደንቦች** 4

3.1 ከእሳት የማስወጣት ሂደቶች 4

3.2 የማምለጫ መንገዶች 4

3.3 ተቀጣጣይ እና ፈንጂ እቃዎች 4

3.4 የቆሻሻ አወጋገድ 4

3.5 የመስክ ስራዎች 5

3.6 ሞቃት ስራ 5

4 **የስጋት ግምገማዎች እና እቅድ አወጣጥ** 5

5 **መቆጣጠር እና ግምገማ** 6

6 **የለውጥ መረጃ** 6

7 **አባሪ I – የሞቃት ስራ ፍቃድ** 6

© Ericsson AB 2021

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ሲሆን ያለ ምንም ማሳወቂያ መለወጥ ይቻላል። ለእውነታዎች ትክክል አለመሆን እና ለህትመት ስህተቶች ኤሪክሰን ሀላፊነቱን አይወሰድም።

# 1 መግቢያ

ይህ ደንብ የጤና እና የደህንነት ጉዳዮች በስርአት እንደተያዙ ለማረጋገጥ በኤሪክሰን ንግድ ላይ ሳሉ የእሳት አደጋዎችን ለመቆጣጠር የሚያስፈልገውን አነስተኛ መስፈርቶች ይገልጻል።

በዚህ ደንብ ውስጥ የአካባቢው ህግ መስፈርቶቹን በሚበልጥበት ጊዜ የአካባቢው ህጋዊ መስፈርቶች ተግባራዊ ይሆናሉ።

# 2 መስፈርቶች

የሚከተሉት መስፈርቶች ተግባራዊ መሆን ያለባቸው:

- ሁሉም አዲስ ሰራተኞች ስለ እሳት የመከላከል እና የድንገተኛ ማስወጣት ሂደቶች የስርጸት ስልጠና ይሰጣሉ፣
- በመስክ ቦታዎች ላይ ማንኛውም ስራ ከመጀመሩ በፊት፣ የተሾመው ሰው ስለ ሳይቱ ሁሉም ሰራተኞች ማወቃቸውን ያረጋግጣል፣
- ሀላፊ የሆነው ስራ አስኪያጅ የተዘጋጁ ድንገተኛ እቅዶች እና የማስወጣት መመሪያዎች ይኖረዋል፣
- ሁሉም የማምለጫ መንገዶች እና የመገናኛ ነጥቦች በምልክት ይለጠፋሉ እና ግልጽ ይሆናሉ፣
- የተቀጣጣይ እና ፈንጂ እቃዎች ቦታ በሳይቱ የድንገተኛ እቅድ ውስጥ ይለያሉ፣
- በማምለጫ መንገዶች ውስጥ በሚነዱ፣ ተቀጣጣይ እና ፈንጂ እቃዎች መዝጋትና እነዚህን ማስቀመጥ (ከደረጃ በታች ያለን ቦታ ጨምሮ) በጥብቅ የተከለከለ ነው፣
- ማንኛውም ከስራ ጋር የተያያዙ ክፍት እሳቶች ወይም የሙቀት ምንጮች ስጋታቸው ተገምግሞ ለሙቀት ስራ ፍቃድ ሂደት ተገዢ ይሆናሉ፣
- የእሳት ኩነት ሲኖር፣ ማንኛውም ስራ በአስቸኳይ ይቋረጣል፣ እና የማንቂያ ደውል ይጮሃል፣
- ሁሉም ሰራተኞች የመገናኛ ነጥቦችን እንዲያውቁ ይደረጋል፣ እና
- እሳት በሚኖርበት ሁኔታ በአስቸኳይ ስምምነት ወደ ተደረገባቸው የመገናኛ ነጥቦች በመውጣት አካባቢው ይለቀቃል።

የቀጠለውን የግል ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ከላይ የተዘረዘረው ከሰራተኛ እና ኮንትራክተር ደህንነት በላይ ቅድሚያ አይሰጠውም።

## 3 ደህንነታቸው የተጠበቀ የስራ ደንቦች

### 3.1 ከእሳት የማስወጣት ሂደቶች

ማንኛውም የእሳት የማንቂያ ደውል የሰማ ሰው:

- ይልቀቅ እና በተዘጋጀው የመገናኛ ነጥብ ላይ ይገናኝ፣ እና
- በሚለቁበት ጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ፣ እሳቱን ዳርቻው ላይ እንዲቆይ ለማድረግ ሁሉንም በሮች እና መስኮቶች ይዝጉ

### 3.2 የማምለጫ መንገዶች

ሰራተኞች ሁሉንም የተሰየሙትን የማምለጫ መንገዶችን፣ የድንገተኛ መውጫዎችን እና የመሰብሰቢያ ቦታዎችን ማወቃቸውን ያረጋግጡ።

ሁሉም የተሰየሙት የማምለጫ መንገዶች፣ የድንገተኛ መውጫዎች እና የመሰብሰቢያ ቦታዎች የተለጠፈ ምልክት እና ህልጽ መሆን አለባቸው። እነዚህ መንገዶች እና መውጫዎች በትንሹ በመረጃ ሰሌዳው ላይ ይታያሉ።

ሌሎች ስፍራዎችን በሚጎበኙበት ጊዜ፣ ሰራተኞች ለስራ ቦታ ቅርብ የሆኑ በትንሹ ሁለት የድንገተኛ መውጫዎች ጋር ራሳቸውን እንዲያስለምዱ እንደሚጠበቅባቸው እርግጠኛ ይሁኑ።

### 3.3 ተቀጣጣይ እና ፈንጂ እቃዎች

ተቀጣጣይ እቃዎች በተሰየመ እና በተፈረመ ቦታ ይቀመጣሉ። የተቀጣጣይ እቃዎች ቦታ በሳይቱ የድንገተኛ እቅድ ውስጥ ይለያሉ እና ምልክት ይደረግባቸዋል።

የጋዝ ሲሊንደሮች (ጠርሙሶች) ቀጥ ብለው ይቀመጣሉ እና አዝምመው ከመቀመጥ ይጠበቃሉ። ባዶ ሲሊንደሮች ከሙሉዎቹ በግልጽ ምልክት መደረግ እና መለየት አለባቸው።

### 3.4 የቆሻሻ አወጋገድ

ኤሪክሰን ውስጥ የሚሰሩ ሁሉም ሰራተኞች ወይም የደንበኛ ሳይት ቆሻሻ አግባብ ባለው ሁኔታ እና በቆሻሻው አይነት  እና የእሳት አደጋ በማያመጣ ሁኔታ በሚወሰነው የአካባቢ መስፈርቶች መሰረት መወገዱን ማረጋገጥ አለባቸው።

### 3.5 የመስክ ስራዎች

የሳይት ድንገተኛ ሂደቶች በደንበኛ ሳይት እና በኤሪክሰን ድንገተኛ ሂደቶች መሰረት ይዘጋጃል።

### 3.6 ሞቃት ስራ

የ 'ሞቃት ስራ' ምሳሌ:

- መበየድ,
- የመበየጃ እሳትን ማቃጠል (ምሳሌ፡ ኦክሲ አሴታይሊን)፣ እና
- የተጋለጡ እሳቶች ሲኖሩ ሌሎች የሚጠቀሙት ምሳሌ የሚፈነዱ የመበየጃ እሳቶች

ሞቃት ስራን የሚያከናውን ማንኛውም ሰው በቂ ልምድ እና ብቃት ሊኖረው ይገባል።

ሞቃት ስራን ከመጀመራቸው ቀደም ብሎ፣ የስራ ቦታዎች ከተቀጣጣይ እቃዎች እና ከሚነዱ ብናኞች/ቆሻሻ መጽዳት አለባቸው።

የሞቃት ስራ ፍቃድ ስራው ከመጀመሩ በፊት ብቁ በሆነ ሰው መሰጠት አለበት። እንደዚህ አይነት ፍቃድ ለተወሰነ ሰአት ብቻ ጥቅም ላይ የሚውልና ከአንድ የስራ ቀን የማይበልጥ መሆን አለበት። ከዚያ በኋላ አዲስ ፍቃድ ማግኘት እና መሰጠት አለበት። የሞቃት ስራ ፍቃድ ምሳሌ በዚህ ሰነድ ውስጥ አባሪው ላይ ሊገኝ ይቻላል።

አንዴ ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የሞቃት ስራ ፍቃዱ ይነሳና አካባቢውን እንዲቆጣጠር በስራው ላይ አለቃ ለሆነው ሰው ይመለሳል።

ተገቢ የሆነ የእሳት ማጥፊያ እና የእሳት ልብስ በሞቃት ስራ ጊዜ መገኘት ይኖርበታል። ለሞቃት ስራ የሚጠቅመው የእሳት ማጥፊያ ከተሰየመው የእሳት ማጥፊያ መወሰድ የለበትም።

ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ በትንሹ ለአንድ ሰአት የእሳት ጥበቃ ያስፈልጋል።

ለሞቃት ስራ ፍቃድ ምሳሌ አባሪውን ይመልከቱ።

## 4 የስጋት ግምገማዎች እና እቅድ አወጣጥ

ሁሉም ስፍራዎች ላይ በመጀመሪያ እና ስፍራው ላይ የእቃ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ ሙሉ የእሳት ስጋት ግምገማ ይደረግባቸዋል። ስራ ከመጀመሩ በፊት ሁሉም የቁጥጥር እርምጃዎች በሙሉ መተግበር እና ለሞቃት ስራ ፍቃድ ሁሉም አቅርቦቶች በቦታው መሆን ይገባቸዋል።

## 5 መቆጣጠር እና ግምገማ

ይህን ደንብ መተግበሩን የሚከተሉትን ነገሮች በመገምገም እና መዝገብ በማስቀመጥ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል:

- የሰራተኛ ስርጸቶች፣
- የስልጠና መዝገቦች፣
- የስጋት ግምገማ
- የእሳት እና መልቀቂያ ቅደም ተከተሎች፣
- የሞቃት ስራ ፍቃዶች፣ እና
- የአጋጣሚ ስታትስቲክስ

## 6 የለውጥ መረጃ

ከመጨረሻው ግምገማ ጀምሮ ያሉ ለውጦች ማጠቃለያ:

1 ጽሁፉን "የመገናኛ ነጥቦች" ላይ ወደ ማምለጫ መንገዶች አንቀጽ ማሸጋገር

2 ቀላል የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ጽሁፍ

## 7 አባሪ I – የሞቃት ስራ ፍቃድ

እባክዎ ቀጣዩን ገጽ ይመልከቱ።

**የሞቃት ስራ ፍቃድ _**

**የሞቃት ስራን ከማስጅመሩ በፊት: ይህን ስራ አለመስራት ይቻላል? ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ አለ?**

**ይህየሞቃት ስራ ፍቃድ የሚያስፈልገው ክፍት እሳቶችን ወይም ሙቀት የሚመነጩባቸው እና/ወይም የእሳት ፍንጣቂ ላለባቸው ማንኛውም ጊዜያዊ ስራዎች ነው። ይህም የሚያካትተው ፣ ነገር ግን በእነዚህ አይወሰንም: መበየድ፣ መቁረጥ፣ መፍጨት፣ ከባድ ብረትን ማያያዝ፣ ቱቦንማቅለጥ,**
**<u>ጣራ ለመስራት እና ለመበየድ የመበየጃ እሳት ተጠቅሟል።</u>**

# አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ጥንቃቄ ዝርዝሮች

**አጠቃላይ**

- ☐ በሞቃት ስራ ምክንያት የእሳት አላርሙን የሚያጠፋው ፍቃድ ያለው ሰው ብቻ ነው። ይህ ሰው የሞቃት ስራው ልክ እንደተጠናቀቀ የእሳት ማንቂያ ደውሉን የማብራት ሃላፊነት አለበት። የእሳት አላርሙ ችግር ሲያጋጥመው የእሳት ጥበቃ በቦታው መሆን አለበት።
- ☐ የሞቃት ስራውን የሚሰራው ሰው አስፋላጊ ስልጠና እና ልምድ አለው።
- ☐ በእጃችን ላይ ያሉ የሚረጩ፣ ቧንቧዎች እና ማጥፊያዎች አገልግሎት ይሰጣሉ/ይሰራሉ።
- ☐ በጥሩ ሁኔታ የተያዘ የሞቃት ስራ መሳሪያ። የመበየጃ መሳሪያው ፍንጣሪውን የሚይዙ እና የማመልሱ ቫልቮች አሉት።
- ☐ የጋዝ ጠርሙሶች በደንብ ይያዛሉ ስለዚህ ለምቶች እና ግጭቶች አይጋለጡም።
- ☐ የጋዝ ጠርሙሶች ጥቅም ላይ ሲውሉ የሞቃት ስራውን የሚሰራው ሰው ድንገተኛ ነገር ሲኖር ጋዙን ለመዝጋት፣ መገልገያዎች እና የመከላከያ ጓንት አለው።

**የ 10 ሜ (33 ጫማ) ስራ መስፈርቶች**

- ☐ ተቀጣጣይ ፈሳሾች፣ ብናኝ፣ ፋሻ እና የዘይት ተቀማጮች ተወግደዋል።
- ☐ በአካባቢው የሚፈነዳ ከባቢ ተቀንሷል።
- ☐ ወለሎች ጸድተዋል።
- ☐ የሚነዱ ወለሎች ረጥበዋል፣ በተጣለ አሸዋ ወይም በእሳት ተከላካይ ወረቀቶች ተሸፍነዋል
- ☐ በሚቻልበት ቦታ ሌሎች የሚነዱ ነገሮች ተወግደዋል። ይህ ካልሆነ ደግሞ በእሳት ተከላካይ ልብሶች ወይም የብረት መከላከያዎች ይጠበቃሉ።
- ☐ ሁሉም ግድግዳ እና የወለል ክፍተቶች ተሸፍነዋል።
- ☐ የእሳት ተከላካይ ልብሶች በስራ ወቅት የተከለከሉ ናቸው።
- ☐ ፍንጣቂዎችን ወደ ሩቅ የሚነድ ነገሮች የሚወስዱ ቦዮች እና ማጓጓዣዎች ተከልክለዋል ወይም ተዘግተዋል።

**ግድግዳዎች፣ ቢላፎኖች ወይም ጣሪያዎች ላይ ስራ**

- ☐ ግንባታ የማይነድ እና የሚነድ ነገር መሸፈኛ ወይም መከላከያ ሳይኖር ነው።
- ☐ በሌላ የግድግዳዎች፣ ቢላፎኖች ወይም ጣሪያዎች ጎን ያሉ የሚነዱ ነገሮች በርቀት ተንቀሳቅሰዋል።

**በተሸፈነ መሳሪያ ላይ ስራ**

- ☐ የተሸፈነ መሳሪያ ከሚነዱ ሁሉም ነገሮች ጸድቷል።
- ☐ ማጠራቀሚያው ከሚነዱ ፈሳሾች/እንፋሎቶች ጸድቷል።
- ☐ በግፊት የተሞሉ እቃዎች፣ ቧንቧዎች እና መሳሪያ ከአገልግሎት ተወግደዋል፣ ተለይተዋል እና አየር ገብቶባቸዋል።

**የእሳት ጥበቃ /የሞቃት ስራ አካባቢ ቁጥጥር**

- ☐ የእሳት ጥበቃ በስራው ጊዜ እና የሞቃት ስራው ከተጠናቀቀ ከ 1 ሰአት በኋላ ይቀርባል፣ የምሳ እረፍት ወዘተ ተካቷል።
- ☐ የእሳት ጥበቃው ተገቢ የሆነ ማጥፊያ ይቀርብበታል፣ ተግባራዊ ሲሆን ደግሞ፣ እና ትንንሽ ቱቦዎች ይሰጡታል።
- ☐ የእሳት ጥበቃው በመሳሪያው አጠቃቀም እና የማንቂያ ደውሉ ድምጽ ላይ ሰልጥኗል።
- ☐ የእሳት ጥበቃው ለሚገናኙ አካባቢዎች ፣ ከላይ እና ከታች፣ ሊፈለጉ ይችላሉ።
- ☐ ስራው ከተጠናቀቀ ከ 4 ሰአት በኋላ የሞቃት ስራ አካባቢውን ይቆጣጠሩ።

☐ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች የተወሰደ:

___________________________________________

<table>
<tr><td>ቀን</td><td>ጊዜ</td><td colspan="3">ስራው የተሰራው<br>☐ ሰራተኛ<br>☐ ኮንትራክተር</td></tr>
<tr><td>ይጀመራል ተብሎ የሚጠበቅበት ቀን</td><td>ይጠናቀቃል ተብሎ የሚጠበቅበት ቀን</td><td colspan="3">ቦታ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የሞቃት ስራውን የሚሰራው ሰው ስም (ፊርማ/በትልቅ ፊደላት)</td><td colspan="3">የስራው አይነት</td></tr>
<tr><td colspan="5">ሞቃት ስራው ስራውን ለማጠናቀቅ የሚገኝ ብቸኛው ዘዴ እንደሆነ ተወስኗል። በአስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ዝርዝር ውስጥ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተወሰዱ፣ ከላይ ያለው ቦታ እንደተመረመረ እና ለዚህ የሞቃት ስራ ፍቃድ እንደተሰጠ አረጋግጣለው።</td></tr>
<tr><td colspan="2">የአካባቢው ተቆጣጣሪ (ፊርማ /ትልልቅ ፊደላት)</td><td>ፍቃዱ የሚያልቀው</td><td>ቀን</td><td>ጊዜ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የእሳት ጥበቃው መተው<br>ፍንጣቂዎች እና ሙቀት ሊሰራጩባቸው የሚችልባቸው የስራ አካባቢው እና ሁሉም በአቅራቢያ ያሉ አካባቢዎች በእሳት ጥበቃው ክፍለ ጊዜ ውስጥ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል (ሞቃት ስራ + 1 ሰአት ተከትሎ ) እና ከእሳቱ ደህንነታቸው የተጠበቀ ሆኖ ተገኝቷል።</td><td colspan="3">የመጨረሻ ምርመራ<br>ከሞቃት ስራው ከ 4 ሰአት በኋላ የስራ አካባቢው ቁጥጥር ይደረግበታል እና ከእሳቱ ደህንነታቸው የተጠበቀ ሆኖ ተገኝቷል።</td></tr>
<tr><td colspan="2">የእሳት ጥበቃ (ፊርማ/ትልልቅ ፊደላት)</td><td colspan="3">የእሳት ጥበቃ (ፊርማ/ትልልቅ ፊደላት)</td></tr>
</table>